# «ግፉ ቢል አዶላ አንሳ ቢል አካፋ» !!

አሥራደው (ከፈረንሳይ) መስከረም 1 ቀን 2002 ዓ.ም.

አወይ ክብረ መንግሥት እንዴት ነው አዶላ ፣

ድሃን እያስራበ መንግሥት የሚያበላ ፣

ባፈሳ በግዞት አፈር እያስማሱ እነሡ ሳይሠሩ ፣

የነገር ልቃቂት ዞትር እያደሩ ፤

አካፋና ዶማ ይዘው ሳይቆፍሩ ፣

ጨለማ መግፈፊያ ሻማ ሳያበሩ ፣

ጠብ ሳይል ላባቸው ባቋራጭ ከበሩ ፤

ያገር አንጡራ ሃብት እየመዘበሩ ፤

በሰው ላብ በሰው ደም ቁጭ ብለው ቆመሩ ::

አፈሩን ሳይዝቁ ጠብ ሳይል ላባቸው ፣

ከጉርጓዱ ገብተው ትንፋሽ ሳያጥራቸው ፣

እጃቸውን አጥፈው እንደተኮፈሱ ፤

ወርቅ አግበሰበሱ ቁጭብለው አፈሱ ::

ተናገር መጋዶ ተናገር ሻኪሶ ፤

ወርቅ ወዴት ተጋዘ ላንተ አፈሩ ደርሶ ፤

ተናገር ሃዲማ ደግሞም ኡላኡሎ ፤

እነማን ዘረፉት የወርቁን አሎሎ ፤

የወርቁን ቡችላ የለገደንቢውን ፤

ደብዛውን ንገሩን የደረሰበትን ::

እነማን ዘረፉት ማንስ ከበረበት ?

እነማን ተዝናኑ ማንስ ጨፈረበት ?

ድሃ በደከመ ድሃ በሞተበት ፤

ጠሙን እንደዋለ አፈር ተንዶበት ::

ደግሞ ፤

አለማፈራቸው ስሙን ሲያወጡለት ፤

አሉት ክብረ መንግሥት ፣

ከድሃ ጉሮሮ ነጥቆ የሚበላ ቀማኛ እንደማለት ::

አልዋሹም ሃቅ ነው ከብሮበታል መንግሥት ፤

ድሃ በደከመ ድሃ በለፋበት ፤

ወርቁን ላመረተ ምንም ሳይሠሩለት ፤

የድሃን ጉሮሮ አንቆ በመቀማት፤

መንግሥት መበዘበረ መንግሥት ከበረበት ::

ግፍ አልበቃ ብሎ ዛሬም እንደ ጥንቱ ፤

ያገር አንጡራ ሃብት ቀጥሎ ስርቆቱ ፤

አንዱ ጅብ ሲጠግብ ሌላው ተተክቶ ፤

ይኸው በዘረፋ ይበላል ተኝቶ ::